*በአገራችን አንድ አባባል አለ። "ህዝብ መሪውን ይመስላል" ይባላል። መሪዎች ፍቅርንና አንድነትን በሚሰብኩበት ጊዜ፤ ህዝቡም በተመሳሳይ ሁኔታ ለሌላው ፍቅርን ይሰጣል። መሪዎች አጉራ ዘለል ወይም ተሳዳቢዎች ሲሆኑ ደግሞ ተከታዮቻቸውም የነሱን ፈለግ ይከተላሉ። እኛ ዛሬ በያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ህሊና ውስጥ መትከል የሚገባን ፍቅርን እንጂ፤ ጥላቻን መሆን የለበትም። ማንም ማንንም ማሸነፍ በማይችልበት ጠርነት ውስጥ ገብተን፤ ዘላቂ የሆነ ጥፋት ከመስራት እንታቀብ... ለዚህም አምላክ ይርዳን።*

*ይህ ጽሁፍ በቅድሚያ የተዘጋጀው በቀድሞ የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር አባላት ስም እንዲወጣ ቢሆንም፤ ከሁለት ሰዎች ወቅታዊ የሆነ ምላሽ ባለማግኘቴ፤ ከሁለት ሳምንታት ቆይታ በኋላ፤ በግሌ ለማውጣት ወሰንኩ።*

ዳዊት ከበደ
(የቀድሞ የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር አባል)

# ይድረስ ለተከበሩ አቶ ኃይሉ ሻወል...

## የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር

ኦክቶበር፣ 2007

በቅድሚያ የከበረ ሰላምታችን ይድረስዎ።

እናንተ የቅንጅት መሪዎች በእስር በነበራችሁበት ወቅት፤ ቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ተመስርቶ፤ በእርስዎም በኩል እውቅና አግኝቶ፤ አስፈላጊውን ድርጅታዊ ስራ ሲሰራ መቆየቱ የሚታወስ ነው። በዚህም መሰረት፤

1ኛ- ህዝቡ ተስፋ ሳይቆርጥ፤ በትግሉ ጠንክሮና ክንዱን አፈርጥሞ በአገሩ ጉዳይ ተሳታፊ እንዲሆን አስፈላጊውን ጥረት አድርገናል ብለን እናምናለን።

2ኛ- ቅንጅትን ወክለን ከውጭ አገር ዲፕሎማቶች ጋር ተነጋግረናል። በተለይም ሎቢና በእድቮኬሲ ስራ ከተሰማሩ ሃገር ወዳድ ወገኖቻችን ጋር በመተባበር ከአሜሪካና ከአውሮፓ ምክር ቤት አባላት ጋር በመወያየት እንደ ኤች.አር. "5423" ያሉ ሰነዶች እንዲወጡ ከዚያም ኤች.አር. "2003" በኮንግረስ ደረጃ እንዲያልፍ ጥረት አድርገናል።

3ኛ- የድጋፍ ድርጅቶች በቅንጅት ዲሞክራሲያዊ መርህ ተገዢ ሆነው እንዲሰሩ አበረታተናል።

4ኛ- የቅንጅትን፣ የመሪዎቹንና የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም የሚነኩ ጉዳዮች በተከሰቱ ጊዜያት ሁሉ፤ ቅንጅትን በመወከል አስፈላጊ መግለጫዎችን ስናወጣ ቆይተናል።

5ኛ- የቅንጅት መሪዎች እንዲፈቱ በተደረገው ጥረት፤ ከኛ ጋር በቀጥታ፤ ነገር ግን በሚስጥር ከአገር ሽማግሌዎች ጋር በመነጋገር፤ ከእስር የምትፈቱበትን ሁኔታ አመቻችተናል።

6ኛ- ከደቡብ አፍሪካ እስከ አውስትራሊያ፤ አውሮፓና እስያ፤ ካናዳና አሜሪካ የሚገኙ የድጋፍ ድርጅቶችን በማጠናከር፤ መሪዎቻቸውን በዲሞክራሲያዊ መንገድ መርጠው እንዲሰሩ አስፈላጊውን ጥረት አድርገናል።

7ኛ- ትንሳኤ ሬዲዮ - ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት፤ የተቃወሙትን ከአባልነት በማስወገድ፤ በወገንተኝነት እየሰራ ቢሆንም፤ የሬዲዮ ስርጭቱ በየቀኑ ወደ ኢትዮጵያ እንዲተላለፍ፤ በተለይም በገንዘብ እጥረት ምክንያት እንዳይቆም፤ ለተከታታይ በርካታ ወራት አስፈላጊውን የፋይናንስ ድጋፍ ስንሰጥ ነበር።

8ኛ- ሻለቃ ዮሴፍ ያዘው ከኬንያ መልስ፤ 250 ሺ.ህ ዶላር ወዳልታወቀ አካውንት፤ በሚስጥር ባዛወረበት ወቅት፤ ከተጠያቂነት ለመዳን ጭምር፤ ቀሪውን ከ30 ሺ.ህ ዶላር በላይ የሚሆን ገንዘብ ከባንክ በማውጣት በቀጥታ ኢትዮጵያ ውስጥና በጎረቤት አገሮች፤ በችግር ላይ ለነበሩ የቅንጅት ቤተሰቦች

አከፋፍለናል። (ባሁኑ ወቅት እንደሰማነው፤ እነሻለቃ ካዛወሩት 250 ሺ.ህና ከሰበሰቡት 54ሺ.ህ ዶላር ውስጥ 12 ሺ.ህ ብቻ አስቀርተዋል፤ ቅንጅት አለም አቀፍ፤ ያዳነው 30 ሺ.ህ ይህን ሁሉ ስራ ተሰርቶበት አራት ሺ.ህ ዶላር አሁንም በአካውንቱ ውስጥ አለ። ይህን የጠቀስኩት ሌላውን ለመውቀስ ሳይሆን ለንፅፅርና ለፍርድ እንዲመች ነው)

9ኛ- የቅንጅት ድረ ገጽ በመክፈት ህብረተሰቡ ነጻ የሆነ መረጃ እንዲያገኝ አድርገናል።

10ኛ- ቅንጅት አለም አቀፍ አመራር በህጋዊ መንገድ፤ በአሜሪካ ህግ መሰረት ተመዝግቦ እንዲሰራ ስናደርግ፤ ከታክስ ነጻ ወይም የ501-C-3 ባለቤት እንዲሆን አድርገናል። በተከታታይ ወራት ያደረግናችውን እንቅስቃሴዎች፤ በተለይም እናንተ ከመምጣታችሁ በፊት ሂሳባችንን በተመሰከረለት የውጭ ኦዲተር አስመርምረን፤ ሴፕቴምበር 17 ቀን፣ 2007 ዓ.ም ለአሜሪካ መንግስት ጭምር ሪፖርት አድርገናል።

ይህ ከላይ የገለጽናቸው ጉዳዮች፤ እናንተ በእስር ላይ በነበራችሁ ወቅት ካደረግናቸው የስራ እንቅስቃሴዎች ጥቂቶቹ ሲሆኑ፤ ከዚህ ውጪ በዚህ ላይ በዝርዝር መጥቀስ የማንችላቸው፤ በውስጣዊ የድርጅት አሰራር የሚገለጹ ተግባራትን አከናውነናለን። የድርጅት፣ የጽ/ቤት፣ የፋይናንስና የአስተዳደር ስነ-ምግባሮችን በመንደፍ ለሁሉም ቻፕተሮች አሰራጭተናል። ለዚህም በተለያዩ ወቅቶች ያደረግናቸው ተግባራት በድምጽ እና በቪዲዮ፤ በሰነድና በፎቶግራፍ ስላሉን ያንን መመልከት በቂ ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ከቅንጅት አለምቀፍ አመራር ጋር በቅርበት የሚሰሩት የድጋፍ ድርጅቶች ድረ-ገጾች የቅንጀትን ራእይና እምነት ከማስራጨት አልፈው የድርጅቱን መሪዎች በተለይም ከቅድመ ምርጫ በፊት እርስዎ በየገጠሩ በመዘዋወር ያደረጉትን ሕዝባዊ ቅስቃሳ ለህዝብ በምስል ይፋ አንዲሆን በማድረግ ከማንም በላይ፤የእርስዎ የአመራር ትልቅነትና ስብዕና ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ አደረጉ እንጂ ወገንና ጎራ ለየተው አንዱን መሪ አንስተው አንዱን ሲጥሉ አልታዩም። ዛሬ ያሉት የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ቢከሰሱም የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ መሪን የአቶ ሃይሉ ሻውልን ተክለ ሰውነት አግዝፈው በማሳየታቸው ካልሆነ በስተቀር እኛም ሆንን የቅንጅት ደጋፊዎች በርስዎ ላይ አንዳችም የጥላቻ ስሜት እንዲኖር አላደረግንም.... በጭራሽ።

ይልቁንም የአለምአቀፍ አማራሩን ሃዘን ያበረታው እነዚህ የድጋፍ ድርጅቶች ወገንተኛ ተደርገው ድካማቸው ጩህኸታቸው ከመጤፍ ሳይቆጠር፤ ሻለቃና ተባባሪዎች በማይታዩባቸው ሰልፎች የሻማ ምሽቶች በብርድ እየተንቀጠቀጡ፤ የመረዎቻቸውን በተለይ ደግሞ የድርጅታቸውን ሊቀ መንበር ምስል ይዘው በጽናት እንዳልቆሙ ሁሉ፤ ይህ ሁሉ ድካማቸው በሚወዱት እና በሚያከብሩት በሊቀ መንበራቸው ተፈርጀ አነሱም የሌሎቹ ወገኖች ተብለው መጠራታቸው ነው። የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ወገንተኛነታቸው ለራሱ ቅንጅት ለቆመለት ዴሞክራሲያዊ መርህ፣ ራእይና አለማ፣ ይህንንም በመሸከማቸሁ አበሳችሁን ላያችሁት ለሁላችሁም ለመሪዎቻችን እንጂ ለአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ሆኖ አያውቅም። በድጋፍ ድርጅቶች

ውስጥ የተጣለው ዴሞክራሲያዊ መሰረት የሰረጸው የዴሞክራሲያዊ ባህል ከእዚህ ውጭ አልነበረም፣ ወደፊትም አይሆንም።

አንድ የመጨረሻ ጉዳይ እናንሳና ደብዳቤያችንን እንቋጫለን።

በቡድን ከተሰራው በተጨማሪ የአለም አቀፉ አመራር አባላት መሃል ጥቂቶቹ ስራቸውን አቁመው ቤተሰባቸውን በትነው ሙሉ ጊዚያቸውን እናንተን ለማስፈታትና ትግሉ እንዲቀጥል ከማድረግ አልፈው የሃገር ቤቱ እንቅስቃሴ በነሻለቃ አሻፈረኝ ባይነት “ገንዘብ የለም” በሚል ሰበብ ችግር ውስጥ በወደቀ ጊዜ የራሳቸውን ገንዘብ ስራ ላይ በማዋል እንዲንቀሳቀስ ለመድረግ ሞክረዋል። ሌሎችም አባለት ከፍተኛ ወጪ ከራሳቸው ኪስ እያወጡ ስራቸውን በማቆም ከአህጉር አህጉር እየተንቀሳቀሱ አለምአቀፍ የቅንጅትን እንቅስቃሴ አስተባብረዋል። እናንተም እንደተፈታችሁ ብዙ ያደነቃችሁት፣ ብዙም ምስጋና የለገሳችሁት በውጭ የሚገኙ የኢትዮጽያውያን ጩኸት አስከምትፈቱ ሳያቋርጥ ለመቀጠል የቻለው አለምአቀፍ አመራሩና የእነ ሻለቃ የሴፍና የተባባሪዎቻቸቸው ስራ እንዳልሆነ በውጭ የሚገኘው ኢትዮጽያዊ የሚያውቀው፤ እናንተም ከመጣችሁ በኋላ የተመለከታችሁት ይመስለናል።

እናንተ እስር ቤት በገባችሁ በአጭር ግዜ ውስጥ የሚያደራጀውና የሚያሰባስበው በማጣት፤ በጥቅምትና በህዳር አንዲያ በከፍተኛ ተነሳስቶ የነበረው ከፍተኛ ቁጥር የነበረው ሃገር ወዳድ በታህሳስ፣ በጥር፣ በየካቲትና በመጋቢት ቁጥሩ እየመነናመነ በሰልፍና በሻማ ማብራት የሚወጡት ግለሰቦች ቁጥራቸው እየተመናመነ፣ ሰለፍና ሻማ መብራቱ የሚደረግባቸው ቀናት እየተራራቁ እንቅስቃሴው ከሞት አፋፍ ላይ ደርሶ እንደነበር መረጃ ማሰባሰብ ይቻላል። ይህ ውድቀት የታየው በግንቦት ወቅት አለም አቀፍ አመራር የሚባል ነገር በትግሉ አድማስ ላይ በማይታይበት ግዜ ነበር። አለምአፍ አመራሩ ከተመሰረተ በኋላም በውሰጥ በነሻለቃ በተከፈተበት ጦርነት ታስሮ ይህንን እየተዳከመ የነበረ ትግል በሚገባው ፍጥነት እንዲያንሰራራ ለማድርግ ባይችልም ለድጋፍ ድርጅቶች መንሰራራት በየቦታው አዳዲስ ድጋፍ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ፣ የተቋቋሙትም በድፍረት እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ወያኔ በሃገር ቤቱ የአምቃ ድርጊቱ የተቀዳጀውን ድል በውጭ እንዳይደገም በማድረግ አለምቀፍ አመራሩ ያደረገውን አስተዋጽኦ፤ እኛ ከምንገልጽ ይልቅ ድካማችንን በቅርብ ሲመለክት የነበረ ኢትዮጵያዊ ምስክርነቱን ሊሰጥ ይችላል።

እንደ እውነቱ ከሆነ፤ የቅንጅት እንቅስቃሴ ብዙሃኑን ያካተተ ድርጅታዊ ቅርጽ እንዲኖረው፤ አለም አቀፍ አመራሩና በአለም ላይ የሚገኙ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተደራጁ የድጋፍ ድርጅቶች በጋራ ባይሰሩ ኖሮ የቅንጅት እንቅስቃሴ በእነሻለቃ ዙሪያ በተሰባሰቡ ሰፊ የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ ለመምራት ብቃቱም ሆነ ህዝባዊ ታማኙነትም በሌላቸው ጥቂት ግለሰቦች እጅ በመውደቅ ያከትምለት ነበር፤ ብለን እናምናለን።

እናንተ በእስር ላይ በነበራችሁበት ወቅት፤ ወያኔ/ኢህአዴግን ሳይሆን አለም አቀፍ የቅንጅት አመራርን ለመጣል፤ ብሎም የድጋፍ ድርጅቶችን ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀት ለማሰናከልና ከተጠያቂነት ለመሸሽ ሲሉ፤ እከዛሬ ማቆሚያ ያጣውንና ስለጡንነት የጎደለውን፣ የሃሰትና የስም ማጥፋት ስራ ሲያካሂዱብን ነበር፤ አሁንም ቀጥለውበታል። የእናንተም ከእስር መፈታት በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተደራጁት የድጋፍ ድርጅቶች የጋራ ስራ ውጤት እንጂ፤ ቅንጅትን ከውስጥ ሲቦረቡሩ የቆዩት ግለሰቦች ለትግሉ ያበረከቱት አስተዋጽኦ እምብዛም እንደሆነ፤ እኛ ሳንሆን ህዝቡ ምስክርነት ሊሰጥበት የሚችል ጉዳይ ነው።

ይህም ሁሉ ሆኖ፤ ስራችንን እንድናቆም የሚገልጸው ደብዳቤ በኦገስት 2007 ዓ.ም ከእናንተ ዘንድ ሲደርሰን የናንተን ትእዛዝ አክብረን፤ ስራችንን አቁመን ከናንተ ተጨማሪ እዝ እየተጠባበቅን ባለንበት ባሁኑ ወቅት፤ በሌላ ወገን የሚገኙ አካላት፤ ከተራ ስድብና ዘለፋ ጀምሮ ድርጅቱን የሚጎዳ ተግባር እየፈጸሙ ይገኛሉ። ይህ በሌላ ወገን እየተካሄደብን ያለውን ዘለፋ በአስፈላጊው መንገድ አፀፋ የመስጠት ብቃቱ እንዳለን ብናምንም፤ ለድርጅቱ ጥቅም በማሰብ ምንም አይነት መግለጫ ሳንሰጥ ቆይተናል። የተለያዩ ሚዲያዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ እንድንሰጥ ጥያቄ ቢያቀርቡልንም፤ ለጊዜው ዝምታን መርጠን የናንተን ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።

እንደ እውነቱ ከሆነ፤ እናንተ ከእስር ቤት ከወጣችሁ በኋላ ግራና ቀኙን በመመልከት እውነተኛውን ፍርድ ትሰጣላችሁ የሚል እምነት ነበረን። በተለይም ሊቀመንበራችን ለሃቅና ለፍትህ የቆሙ ናቸው የሚል እምነት ስለነበረን፤ ከአገር ቤት ጀምሮ እዚህ አሜሪካ እስከሚመጡ ድረስ በስልክም ሆነ በአካል ልናገኛችው ጥረት ብናደርግም፤ በዙሪያቸው በሚገኙ፤ በእኛንም ላይ ስር የሰደደ ጥላቻ ባላቸው ግለሰቦች ምክንያት፤ አንድም የቀድሞ የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ሊያገኛቸው አልቻልንም።

ይልቁንም አቶ ኃይሉ ሻወል የአሜሪካ ድምፅን ጨምሮ፤ በተለያዩ ሚዲያዎች በመቅረብ እኛን እንደጥፋተኛ በመወንጀላቸው በእጅጉ አዝነናል። ላለፉት አመታት ለድርጅቱና ለህዝቡ ያደረግነውን ጥረትና ድካም ከንቱ በሚያስቀር ሁኔታ የማያቋርጥ ዘለፋዎች እየደረሱብን ነው።

ባለፈው አመት እሁድ - ኦክቶበር 15 ቀን፤ 2006 ዓ.ም “አመጣጡ የማይታወቅ ቅንጅት አለም አቀፍ አመራር የሚል አካል አቋቁመዋል” በሚል በሻለቃ ዮሴፍ ያዘው ፊርማ፤ የድርጅቱን አባላት ከማባረር አልፎ ገንዘብ የማባከን፣ የማሸሽና የድርጅቱን አርማ በግለሰብ ስም እስከመመዝገብ ደረጃ ድረስ ተደርሷል። “ይህ ሁሉ ድርጅታዊ ግድፈት ከልዑካን ቡድኑ ጋር በመነጋገር ይፈታል” የሚል እምነትና ተስፋ ነበረን፤ ሆኖም ግን ይህ ተፈጻሚ ሊሆን አልቻለም።

አሁንም ለተከበሩ አቶ ኃይሉ ሻወል የምናቀርበው አቤቱታ ቢኖር፤ እርስዎ ባልፈጸሙት ተግባር በሃሰት እንደተወነጀሉት ሁሉ፤ ፍትህን አጥተው በእስር ላይ እንደቆዩ ሁሉ፤ እኛም በሀሰት ተወንጅለንና ድርጅታዊ ፍትህ አጥተን እንገኛለን። በመሆኑም በኛ ላይ በሃሰት የሚደረገው ተራ የስም ማጥፋት ቆሞ፤ ቢያስፈልግ እርስዎ ብቻዎን ወይም ከልዑካን ቡድኑ ጋር በአንድነት ሆነው፤ በኛ በኩል ያለውን ሪፖርት እንዲያደምጡ እንፈልጋለን። ከዚህ ሪፖርታችንም በኋላ ምስጋናው ቢቀርብን፤ በፍቅር ያሰናብቱናል የሚል እምነት አለን። በእርግጥ ያጠፋነውም ካለ፤ እርስዎ እንደ አባት የምንመለክትዎ መሪያችን በመሆንዎ፤ አባት ለልጁ እንደሚያደርገው ሁሉ እንዲመክሩንና እንዲገስጹን እንሻለን። በዚህ የትግል ወቅት ያስቀየምነው ግለሰብና ቡድን ካለም ለድርጅታችን ስንል፤ ይቅር ለማለት ዝግጁ ነን።

ከዚህ ውጪ ግን ቢያንስ አንዳችንን እንኳን አግኝተውን ሳያነጋግሩን፤ በሌላ ወገን ያሉትንና በኛም ላይ በሚያሳዝን ሁኔታ የሃሰት ምስክርነት የሚሰጡትን ሰዎች በማድመጥ የሚደረጉ አስተያየቶች ለድርጅታችን ፈጽሞ አይጠቅመንም። ዛሬ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀው በአንድነት፤ ለአንድ አላማ ቆመን ለአገራችንና ለህዝባችን መስራት ነው።

አሁን በደጋፊዎቻችን መካከል የተጀመረው አይነት አሉባልታ በቸልታ ከቀጠለ፤ ድርጅቱን ከተግባር ይልቅ የወሬ ፋብሪካ ያደርገዋል። ይህን እንደባህል የምንከተል ከሆነ ደግሞ፤ ይዋል ይደር እንጂ፤ ዛሬ ከጎናችን ያሉ የሚመስሉን፤ ነገ ከነገ ወዲያ ሲያኮርፉ፤ የአሉባልታ ዘመቻቸውን በእርስዎም ሆነ፤ በሌሎች ለአገራቸውና ለህዝባቸው የሚሰሩ ዜጎቻችንን መቀጠላቸው የማይቀር ነው። ታዲያ ይህንን ማቆም የሚቻለው፤ መሪ “ተው” ማለት ሲችል እንጂ፤ አይቶ እንዳላየ በማለፍ አይደለም።

በመሆኑም ስለ ድርጅቱ፤ ስለሚወድዎ ህዝብና ደጋፊዎቻችን ብለው፤ ቅንጅትን ወደ ነበረበት ዝናው እንዲመልሱት እንጠይቃለን። ይህንን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ በቀድሞ የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር በኩል ያለውን ሪፖርት በጽሞና ማዳመጥ ሲቻል ነው። ለዚህም ቀጠሮ እንዲይዙልን ከአክብሮት ጋር እንጠይቃለን❑